# <u>እጹብ ድንቅ ሃሳብ ፤ ሆኖም ጋሪዉን ከፈረሱ ማስቀደም አይሆንም?</u>

## በፈቃደ ሸዋቀና የፖለቲካ እርቅ ሃሳብ ላይ አስተያየት

ሰለሞን ገ/ስላሴ

ፈቃደ በቅርቡ "የስደቱን መከራ ወደ መፍትሄ መፈለጊያ እድልነት መቀየር ይቻላል? የመነሻ ሃሳቦች" በሚል ርእስ አንድ ድንቅ ጽሁፍ አቅርቧል። ጸሃፊዉ ለዚህ ዋናና ተዛማጅ ችግሮቻችን እንደመፍትሄ ያቀረበዉ ብሄራዊ እርቅ መፍጠርን ነዉ። በፈቃደ እይታ ፖለቲካዊ እርቅ የፖለቲካ መረጋጋትን ያሰፍናል፤ ስለሆነም ሰላምና እርቅን የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን መፍጠር ያስፈልጋል።

ጸሃፊዉ ለዚህ ተገቢና ትክክለኛ ሃሳቡ ተፈጻሚነት በዋናነት የተሞረኮዘዉ በስልጣን ላይ ያለዉ ወያኔ/ኢህአደግን ሊያሳምኑ ይችላሉ ተብለዉ በሚገመቱ ሃሳቦች ላይ ነዉ። አንባቢ እንደሚረዳዉም ይህን ሃሳብ ከሃሳብነት ወደተግባር ሊለዉጥ የሚችለዉ ባመዛኙ መንግስት በመልካም ፈቃዱና አገሪቱ ወደፊት ሊደርስባት የሚችለዉን አደጋ ግምት ዉስጥ በማስገባት ነው። ፈቃደ፤ መንግስት በዚህ በኩል ሊያጤናቸዉ ይገባቸዋል ያላቸዉን ድንቅ ድንቅና መሬት ላይ የማይወድቁ ሃሳቦችን በምክር መልክ አቅርቧል።

ሃሳቤ "የተሟላ ለመሆን ብዙ ዉይይት ይጠይቃል" ባለዉ መሰረት በበኩሌ የሚሰማኝን እንሆ ከዚህ በታች አቀርባለሁ። አገራችን በልማትና በስልጣኔ ወደፊት እንድትራመድ የሳይንስና የሂሳብ ትምህርቶችን ማስፋፋትና ግኝቶችን መጠቀም፤ ምርምር ማበራከት ይጠበቅባታል። ከዚሁ በማያንስ ደረጃ ደግሞ የፖለቲካ ታሪክ ትምህርትን አስፈላጊነት ዜጎች እንዲረዱት ማድረግና ግንዛቤም መፍጠራቸዉ የግድ ነዉ። ተደጋግሞ እስኪሰለች ድረስ እንደተባለዉ ካለፉ ክስተቶች ያልተማሩ መልሰዉ ስህተቶችን ይደግማሉ።

የራሳችን አገር ያለፉት ሶስት አስርታት ሊሞላቸዉ የተቃረቡ ታሪኮችና (ወያኔ/ኢህአደግ ወደስልጣን ከመጣ) የዘመናዊ አለም አቀፍ ታሪኮችን ስንቃኝ፤ አገሪቱን በሚቆጣጠር አምባገነናዊ መንግስትና በተገዥዎች መካከል ያለዉ የሃይል ሚዛን መቀራረብ ለፖለቲካ እርቅ መሳካት ቁልፍ ጥያቄ ነዉ። ይህ እንግዲህ በተቀዳሚነት የፈቃደን አመክንዮአዊ አቀራረብ ዉድቅ ያደርጋል ማለት ነዉ። መንግስት፤ ወያኔም ሆነ ሌላ አምባገነን መንግስት፤ ስልጣኑን መከታ በማድረግ ስልጣን የሚሰጣቸዉን ጥቅሞች ሁሉ ለብቻዉ ተጠቃሚ ሆኖ ለመቀጠል ባለዉ ፍላጎት ለ አመክንዮ ክፍት ጆሮና ህሊና የለዉም። ነገን ማየት የሚችለዉ በዛሬ አይን ብቻ ነዉ። ነገን እንደዛሬዉ ለማስቀጠል የሚችለዉን ሁሉ ያደርጋል። በስሩና በቁጥጥሩ የሚገኙትን የወታደር ሃይል፤ የፖሊስና የጸጥታ ሃይል፤ ፍርድ ቤቶችንና ያገሪቱን ሃብት ሁሉ ለዚህ ኢሞራላዊና ወንጀለኛ ተግባር ያዉላል። በታሪክ ከዚህ ድርሳን ዉጭ ፖለቲካዊ ድርድር የተደረገባቸዉ እኔ የማዉቃቸዉ አንድ ወይም ሁለት ክስተቶች ናቸዉ። እነዚህም አምባገነኖቹ የራሳቸዉን አቅም አጋንኖ በማየትና ምናባቸዉ እዉነት መስሏቸዉ ህዝብን በእዉነተኛ ምርጫ ሲፈታተኑና ዋጋቸዉን ሲያገኙ የታየበት ነዉ። ጥሩዉ ምሳሌ አምባገነኑ የቺሌዉ ፒኖሸት በራሱ ያለቅጥ በመተማመን በ 1988 ኢ.ም. "አገዛዜ ይቀጥል ወይስ አይቀጥል?" "አዎ፤ወይም አይሆንም" በሉኝ ብሎ የቺሌ ህዝብ ሎተሪ እንዲያቸንፍ የረዳበት ክስተት ነዉ። ለዚያዉም ቢሆን አማራጭ ሃሳብ ብየ ከታች እንደማቀርበዉ የቺሌ ህዝብ በፖለቲካ ፓርቲዎቹና ግምባሮቹ ስምረት ታቅፎ እልህ አስጨራሽ ትግል በማድረጉ ነዉ አምባገነኑን ፒኖሸን አስገድዶ የተሳሳተ እልህ ዉስጥ የከተተዉ። ተቸንፎም ስልጣን ወዲያዉ አልለቀቀም።

የፖለቲካ እርቅን አስመልክቶ የራሳችን ታሪክም እንኳን ለኛ ለሌላም ይተርፋል። የመጀመሪያ ሙከራዉ በ 1993 ኢ.ም. አዲስ አበባ ዉስጥ በግዮን ሆቴል ከዉጭ በ ኢትዮጵያ ደሞክራሲያዊ ሃይሎች ቅንጅት፤ በአነግ፤ በመድህን ወዘተ ተሳታፊነት አገር ቤት ዉስጥ እንደ ደቡብ ድርጅት፤ መአህድ በመሳሰሉ የፖለቲካ ድርጅቶችና እንደ መምህራን ማህበር በመሳሰሉ የሲቪክ ድርጅቶች የተደራጀዉና የተካሄደዉ የእርቅ ሙከራ ነዉ። ወያኔ/ኢህ አደግ በ እርቁ እገኛለሁ ብሎ ለድርጅቶቹና ለዉጭ ታዛቢዎች ቃሉን ቢሰጥም፤ እንኳን ሊገኝ፤ የጉባኤዉን ተሳታፊዎች በማሰር እርቁ እንዳይሳካ የከለከለበት ስብሰባ ነበር። ከዚህ የተገኘዉ ትምህርት፤ አስገድዶ እንኳን ስብሰባዉን አዲስ አበባ ለማድረግና "ጠረኛ" የተባሉ የዉጭ ድርጅቶችን እንዲገቡ ለአፉም ቢሆን መፍቀድ የተገደደዉ <u>ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች፤ ከብሄር ድርጅቶች እስከ ብሄር አቀፍ ድርጅቶች፤ የሲቪክ ድርጅቶችና ታዋቂ ግለሰቦች በጋራ እንደ አንድ ሰዉ ለመቆም በመቻላቸዉ ነበር።</u>

ይህዉ ስብስብ አማራጭ ሃይሎችን አቋቁሞ፤ በኋላም በኢትዮጵያ ፖለቲካ ዝግመተ ለዉጥ ሂደት በሌሎች ህብረቶች የተተካ ነዉ። ከዚህ ቀጥሎ አቢዩ በመንግስትና በፖለቲካ ተቃዋሚዎች መካከል የተደረገዉ ዉይይት

ምርጫ 2005ን ተከትሎ ነበር (1997 እንደ ኢትዮጵያ)። በዚህ ወቅት ከሁለቱ ጠንካራ ስብስቦች አንዱ የነበረዉ የ ኢትዮጵያ ደሞክራሲያዊ ሃይሎች ህብረት ወኪሎች እነ ዶ/ር መረራና በየነ ከመለስና በረከት ጋር ያደረጓቸዉ ጥቂት ዉይይቶች ናቸዉ። "ምርጫ ቦርድ ይለወጥ አትበሉ እንጂ ሌላዉን ሁሉ መወያየት እንችላለን" ብሎ የጀመረዉ መለስ፤ አንዳንዴ በትህትና ብዙ ጊዜ ግን በማስፈራራት፤ ዉጭ ያሉ የህብረቱ አባል ድርጅቶች እንኳን ገብተዉ እንዲሰሩ እስከመናገር ደርሶ ነበር። ምርጫ 2005 በምን ሁኔታ እንደተፈጸመ ሁላችንም በአዘኔታ ስለምናስታዉሰዉ ወደ ዝርዝሩ አንገባም።

ግን አሁንም መለስና ፓርቲዉ ኢህአደግ ለዚህ ቅድመ ምርጫ ከተቃዋሚዉ ጋር ዉይይት እንኳን ላይ የተደረሰዉ በወቅቱ የነበሩት ተቃዋሚ ድርጅቶች ቢያንስ በሁለት ትልቅ ሰፈር ዉስጥ ተሸጋሽገዉና ተደራጅተዉ ስለነበረና ድር ቢያብር አንበሳ ያስር የተባለዉ እዉነታ የፈጠረዉ ሃቅ ነበር። ይህ ሃቅ ደግሞ እንደ አፓርታይድ ደቡብ አፍሪካ ባሉ አገሮችም ታይቷል። ቤተክርስቲያንና መስጊድ፤ ሲቪክ ድርጅቶች፤ የሙያ ማህበሮችና የፖለቲካ ድርጅቶች እንደ አንድ ሰዉ በጋራ ሲቆሙ፤ አለም አቀፍ ድጋፍም ታክሎበት አፓርታይድ የተሸነፈበትን ሁኔታ በህይወት ኖረን ለማየት በቅተናል።

ከ2005 ኢ.ም. በኋላ ላለፉት አስር አመታት የሆኑትን ተመልሰን ብናስታዉስ፤ በወያኔ/ኢህአደግ በኩል እንኳንስ የብሄራዊ እርቅን ሃሳብ ሊቀበል ቀርቶ እንዲያዉም የፖለቲካ ምህዳሩን በማጥበብ፤ በድርጅቶች ዉስጥ መከፋፈል እንዲፈጠር በማበረታታት፤ ገሚሶችን የምርጫ ስነምግባር ፈራሚዎች ናችሁ ብሎና አስፈርሞ ማባበል፤ ጋዜጠኞችንና የህዝብ ወገኖችን ማሰርና ማሰቃየት ነዉ።
ፈቃደ "እኔ ችግር ማዉራትና ማማረር የሰለቸኝ ሰዉ ነኝ" ይላል። እዉነት ነዉ። ግን ወደምንፈልገዉ ግብ ለመድረስ የታሪካችን ክፍል የሆነዉን ችግር ማስተዋልና መተንተን ትክክለኛ መፍትሄ ለማግኘት ያስችላል። ባለፉት አስር አመታት ድርጅቶቻችን እንደ ግመል ሽንት ወደ ኋላ ሲሄዱ፤ ከመሰባሰብ፤ መለያየት ሲቀድም፤ ሁለተኛና ሶስተኛ መሆን ያለባቸዉ ልዩነቶች አንደኛ ልዩነት እየሆኑ፤ አስከትለዉም በአንደኝነታቸዉ ህብረት እንዳይፈጠር፤ የተፈጠረዉም ህብረት እንዳይጠናከር እያወኩ፤ ህዝባችንን ለማሳዘንና የትግል ፍላጎቱን ለማብረድ አስተዋጻኦ አድርገዋል።

ከላይ እንዳልኩት በመንግስትና በተቃዋሚዎቹ መካከል የሃይል መቀራረብ ሲፈጠር ለፖለቲካ እርቅ ዉይይት አመቺ ሁኔታ ይፈጠራል። ይህ የሃይል መቀራረብ ግን እንዴት ይፈጠራል የሚለዉን ማየት አግባብ አለዉ።

አንደምገምተው ብዙዎቹ የፈቃደ እርቅ ሃሳብ ተቃዋሚዎች የሃይል መቀራረብ በሚለዉ ንድፍ ሃሳብ ይስማሙ ይመስለኛል። ግን አብዛኞቹ የሚያምኑት ይህ መመጣጠን በመሳሪያ ሃይል ብቃትና ዉጤት ነዉ ብለዉ እንደሚያምኑ እገምታለሁ። እኔ ይህ የትግል ስልት ሁለተኛ እንጂ ዋነኛ አይመስለኝም። እኔ ባላምንበትም ብዙዎቹ በዚህ የመሳሪያ ትግል አምነዉ ተሰማርተዉበታል። ይህ ከፋት ባልኖረዉ። እንቅፋት የሚፈጠረዉ በአንደኛነት መቆም ስለሚገባዉ የሁሉንም አይነት ድርጅቶች በጋራ መቆምና ድንኳኑ ዉስጥ አብሮ መስራት፤ የትግል ስልት ምርጫ አዋኪና እንቅፋት ሲሆን ነዉ።

በዉጭ በኩል ሁለገብ ትግል የሚሉና ሰላማዊ ትግል ላይ ያተኮሩ የፖለቲካ ድርጅቶች፤ የሰብ አዊ መብት ተሟጋቾች ፤የብሄር ተሟጋቾችና የዲፕሎማሲ ተሟጋቾች ወዘተ ይገኛሉ። ወያኔ/ኢሃደግን ወደ ፖለቲካ እርቅ ዉይይት ለማምጣትና ብሄራዊ እርቅ ለመጀመር የሃይል መመጣጠን/መቀራረብ ያስፈልጋል ካልን፤ በዉጭ በኩል ያለዉ ሰፊ ህዝብና ድርጅቶቹ በአንድ ድንኳን ዉስጥ ሰፍረዉ ለመስራት መቻል አለባቸዉ። ይህ እስካሁን አልሆነም። ይህ ቢሆን፤ ለአገር ቤቱ ትግል ተስፋ ይሰጣል፤ የታጋዩን ቁጥር ያበራክታል፤ የታሰሩ አርበኞቻችንን ዘመዶች በገንዘብ በቋሚነት መደጎም ይቻላል፤መከራ ሲመጣብን ብቻ ሰልፍ ከመዉጣት በእቅድ በአመት የተወሰኑ ቀኖችን የትግል በአሎች በማድረግ ህዝብን አስተባብሮ ባንድነት ማዉጣት ይቻላል፤ በዲፕሎማሲዉም በኩል ከበሬታንና ክብደትን ማግኘት ይቻላል፤ ከላይ ከታሪካችንም እንዳየነዉ ፤ወያኔ/ኢህደግ የተባበረ ጉልበትን ቢያንስ ለማዳመጥ ይሞክራል።

ይህ ቁልፍ ጥያቄ ህብረት ሳይፈጠር እንደተለመደዉ በትንንሽ ድሎችና ክንዋኔዎች እየረካን ለምሳሌ የፖለቲካ ድርጅቶችን የህዝብ ስብሰባ መጥራት፤ እንደ ኢሳት ላሉ አስፈላጊ የመገናኛ ብዙሃን ገንዘብ ስብሰባ ማድረግ፤ አልፎ አልፎ ኮንፈረንስ ማድረግ፤ አሁንም አዲስ ዉርደት ሲፈጠር ተሰባስቦ ላንድ ሳምንት ሃዘን መድረስ፤ ወዘተ ትልቁን ስእል ማየትና ህብረት መፍጠር ካልቻልን የፖለቲካ እርቅ ከምናባዊነት ዉጭ ተፈጻሚነት አይኖረዉም።

ባገር ቤት ያለዉም ዉጭ ካለዉ ሁኔታ የተሻለ አይደለም። እንዲያዉም ዋና የትግል መስክ በመሆኑ የድርጅቶቹ

*መፈራቀቅ ይበልጥ ያማል። ከ ቅንጅትና ህብረት ክስመት በኋላ የተፈጠረዉ ፌዴራላዊ መድረክ ድርጅቶችን በማሰባሰብ ተስፋ ተጥሎበት ነበር። ወያኔ/ኢህ አደግም ይህ ሁኔታ አደገኛ ስለመሰለዉ መድረክን ለመጥለፍ በ 2010 ምርጫ የስነምግባር ሰነድ ካልፈረምክ ብሎ ቁም ስቅሉን አሳይቶት ነበር። ተስፋ የተጣለበት መድረክ አንድነት ከዉስጡ ሲወጣና በኋላም ሰማያዊ ፓርቲ በራሱ ሲሄድ፤ ለወያኔ/ኢህ አደግ ሰርግና ምላሽ ሆነለት። አንድነትም በርትቶ መዋቅሩን በመላ አገሪቱ ሲዘረጋ የወያኔ/ኢሃደግ ፍርሃት እንደገና አገረሸና ጨርሶ ድምጥማጡን አጠፋዉ። ብዙ ድርጅቶችን አሰባስቦ የነበረዉና ወያኔን ያስጨነቀዉ ፌዴራላዊ መድረክ ሲዳከም፤ ወያኔ/ኢህ አዴግ ታክቲኩን በመለወጥ፤ በ 2015 ምርጫ ዋዜማ አንድነትንና ሰማያዊን አክራሪ አድርጎ ለማሳየት እነሱ የጠሩትን ሰላማዊ ሰልፎች ሲያዋክብና ሲበትን፤ መድረክ የጠራዉን ሰልፍ በሚቆጣጠረዉ መገናኛ ብዙሃን ወያኔ ቡራኬ ሲሰጠዉ ተስተዉሏል። በመድረክ ዉስጥ የ አረና ትግራይ ፓርቲ መኖር እጅግ ጠቃሚ ክስተት ነዉ። ወያኔ/ኢህ አደግ የጎሳ ልዩነት እየፈጠረና ለትግራይ ህዝብ "መጡብህ" እያለ ለሚያደርገዉ ሃላፊነት የጎደለዉ ማስፈራሪያ ማርከሻ መድሃኒት ነዉ። የኢትዮጵያ ህዝብ፤ እገሌ ከእገሌ ሳይባል፤ ሁሉም የህግ የበላይነት ጥማት እንዳለባቸዉና ዴሞክራሲያዊ መንግስትን እንደሚሹ ህያዉ ማስረጃ ነዉ።*

*ለተቃዋሚ ድርጅቶች አለመተባበር አንዱ ምክንያት ለብቻ "አዉራ ፓርቲ" የመሆን አባዜ ሊሆን ይችላል። የ "አዉራ ፓርቲ" ጽንሰ ሃሳብ እንኳን በአምባገነንነት ለሚዳሽቅ ህዝባችን፤ ነጻነት ላገኙት ለነ ደቡብ አፍሪካም አልበጀ። አዉራ ፓርቲዉ (ANC) ሙስኛና ለሰፊ ድሃ ህዝቦች ተቆርቋሪ የማይሆንበት ሰፊ እድል ይፈጠራል። ኢሃደግም ቢሆን "አዉራ ፓርቲ" ስለሆንኩ ነዉ ተደጋግሜ የምመረጠዉ " የሚል የሃሰት ፕሮፓጋንዳ ይነዛል። በጋራ መስራትና የተለያዩ እይታ ያላቸዉን ፓርቲዎች ሃሳብ አብሮ ማበራየትና መመርመር፤ ፍቱን የሆኑ ድንቅ ሃሳቦች የሚፈልቁበትና የተደላደለ መንግስት የሚመሰረትበትን ጎዳና ይጠርጋል። ከዛሬ የተጀመረ ጠንካራ ህብረትና አብሮ መስራትም ለወደፊት በዴሞክራሲያዊ ስር አት ለሚመሰረት የ coaltion /ቅንጅት መንግስት የመተዋወቅና አብሮ የመስራትን ባህል ያዳብራል።*

*ለአገር ቤት ህዝብ ተቃዋሚ ድርጅቶቹ ወያኔን በማስገደድም ይሁን በማሳመን ለምን ዴሞክራሲያዊ ስር አት ለመፍጠር እንደማይስማሙና አለን የሚሏቸዉን ልዩነቶች በዴሞክራሲያዊ ስር አቱ ዉስጥ ያኔ እንደማይፈቱ ግልጽ አልሆነለትም። በዚህ ላይ ግልጽ አለመሆን ደግሞ ዋጋ ያስከፍላል። ወደ ትግሉ የሚቀላቀለዉ ቁጥሩ ይመናመናል፤ የተቀላቀለዉም መስዋእትነትን ለመድፈር ሁለት ጊዜ ያስባል። በህዝባዊ መነሳሳት ወያኔ/ኢህ አደግን ወደ ዉይይት ለማምጣት እየከበደ ይሄዳል። ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ የምናየዉም የትግል ዳተኝነት ከዚህ ባመዛኙ የመነጨ ነዉ ማለት ይቻላል። እንዲያዉም የተቃዋሚዎች ህብረት አሳዛኝ ሁኔታ፤ጥቂት ስር አቱ የተመቻቸዉ የሚሉትን "ካልታወቀ መል አክ የምታዉቀዉ ሰይጣን" የሚሉት የተሳሳተ ግለኝነት በህብረተሰቡ ዉስጥ ስር እየሰደደ ይሄዳል። ይህ የተፋዘዘ ሁኔታ ደግሞ የዜግነት ግዴታቸዉን በቅጡ ለማይወጡ አንዳንድ ወስላቶች ጭምር ተቃዋሚ ፓርቲዎችን "የተለየ አማራጭ ፖሊሲ የላቸዉም" "አይታገሉም እኮ" እያሉ በሃሰት እንዲያንቋሽሿቸዉ በር ይከፍታል።*

*ወያኔ/ኢህ አደግ መሳሪያ፤ ገንዘብ፤ ሰራዊትና አለም አቀፋዊ ድጋፍ ቢኖረዉም፤ ህዝብና ተቃዋሚዎች ከሱ በእጅጉ የበለጠ እምቅ ሃይል አላቸዉ። የህዝብ ድጋፍ። ይህ ፕሮፓጋንዳና ባዶ ምኞት አይደለም። በ 2005 በተሰረቀ ምርጫ በታሪክ ፊት ታይቷል። ታዲያ ይህን የ ሃይል መመጣጠን ለመፍጠርና ወደ ብሄራዊ እርቅ ለመምጣት ይህን የህዝብ ድጋፍ ለብቻ ሮጦ ለማግኘት መሻት ሳይሆን፤ ባንድነት በሁለት ትልልቅ ድንኳን ዉስጥ፤ አንድ ባገር ቤት በሚተከል፤ አንድ ዉጭ በሚተከል ዉስጥ ተሸጋሽጎና ተደራጅቶ፤ የበሰለ ስትራተጂና ታክቲክ እያወጡ መታገልን ይጠይቃል። ወያኔ/ኢህ አደግ ከተቃዋሚ ድርጅቶችና ከሚደግፋቸዉ ህዝብ አንድ እርምጃ ሁሌም ወደፊት ነኝ ብሎ እስካመነ ድረስ (ጠንካራ ህብረት እስካልተፈጠረ ደግሞ ይህ እምነት ይቀጥላል)፤ በወያኔ ሰፈር የፖለቲካ እርቅ ሃሳብ መቀበል ከቶ የማይታሰብ ነዉ።*

*በሌላ በኩል ፈቃደ እርቁ ተቀባይነት እንዲኖረዉ ይረዳል በሚል ስሌት ይመስላል "በተቃዋሚዎች በኩል አሁን በስልጣን ላይ ያሉ ግለሰቦች ያፈሩትን ሃብትና ጥሪት ካለምንም ጥያቄ እንዲጠቀሙበትና ለቤተሰባቸዉም እንዲያወርሱት ዋስትና በሚሰጥ ሁኔታ ማረጋገጥ..." የሚል አሳብ አቅርቧል። ይህ አስቸጋሪና ሙስናን በቀጣይነት ባገራችን ችግር እንዲሆን የሚጋብዝ ሃሳብ ይመስለኛል። አጣሪ ኮሚቴ ተቋቁሞ በሙስና የተገኘ ንብረት ካለ ወደ ህዝብ፤ የጠፋዉና በእጅ ያልተገኘ ሃብት በምህረት የሚለዉ ማስታረቂያ ሊሆን ይችል ይሆናል። የድሃዉ ቁጥር የት እየሌሌ በሆነባት ኢትዮጵያችን፤ በሙስና የተገኙ ህንጻዎችንና ቋሚ ንብረቶችን በይርጋ ለባለስልጣኖች መተዉ ከሞራል አንጻርም ፈታኝ ነዉ።*

**በማጠቃለያ ጠንካራ ህብረት በሌለበት ስለ ብሄራዊ እርቅ ማዉራትም ሆነ ታላቅ ዴሞክራሲያዊ ድል ከትንንሽ የተናጠል ድሎችና ክንዋኔዎች መጠበቅ ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ ይሆንና የሸንፈት ታሪካችንን አመት አልፎ አመት ሲተካ እየደገምንና እየሰለስን እንኖራለን። ወጣቱ ትዉልድ ስቃዩ እየተበራከተ እንጂ እየቀነሰ እንደማይሄድ በርግጠኝት መናገር ይቻላል።**

**አሳዛኙን ሁኔታ ለመለወጥ ግን መፍትሄዉና ቁልፉ በእጃችን ላይ ነዉ።**

**ጁን 2015**